# ሕግ በምህረት ሲሸፈን

ተኮላ መኮንን
Tekola Mekonen

አመድ የሸፈነው ፍም፣ አናቱ የደረቀ ቁስል፣
ላዩ የቀነበር ዳቦ፡- ያልበሰለ ግንፍልፍል፣
ተበልቶ ጤና ሊነሳ፡- ሲነካ ቆይቶ ሊያቃጥል፣
ብስና እየተነነ ጋዝ እየፈጠረ ሊበክል።

የረገጠውን ሊያንገበግብ፡ የጨበጠውን ሊለመጥጥ፣
እንኳን ለዓይን ምስክር ለሰማሁ ሁሉ ሊሰነፍጥ።
በምሕረት ካባ ላይሸፈን በፍቅር በርኖስ ላቀበር፣
በእምነት ጥላ ላይጠለል በይቅርታ ላይታጠር።
ስሙ ተቀያይሮ ገዳይነቱ ባይወሳ፣
ዓመታት ቢያልፉም ግፍ መሆኑ አይረሳ።

ካሚሚትም አሚሚት ብልት አካሉ ተቆርጦ፣
በፈላ ዘይት ተጠብሶ በሽቦ ባለንጋ ተለምጥጦ።
ዓይኑ በጉጠት ወጥቶ ጥፍሩ በወረንጦ ተነቅሎ፣
በጉድጓድ በአንድነት ታጉሮ በጥይት እሩምታ ተበታትኖ።
ለሞተ ወጣት ካልቆምን በግፍ ለተገደለ፣
የተጀመረው ምኑን ትግል ተባለ።

ምንድነው እሱ ምሕረት እጁ በደም ሲበከል፣
የእናት ለቅሶ የአባት ሐዘን ወይኔ ልጄ ሲከለከል።
የት ነበሩ አባቶቹ? ስበካን የጀመሩን፣
ሲገድሉ ሳይናገሩ ዛሬ ምሕረትን የሚያስተምሩን።

ትላንት ገዳዮቹን እንደ ፈሯቸው፣
ዛሬም መታሰራቸው ቀፈፋቸው፣
አንቱ ባሉበት አፋቸው አንተነታቸው አስፈራቸው፣
በሞቱት ላይ ፈረዱና ገዳዮቹን አስለቀቋቸው።

መንግስትም መመሪያውን አነበጠ፣
እስረኞቹን በጓሮ በር አስመለጠ።
ተቃራኒ ሃሳብ ፈጠረ
ገሚሱን በሕግ ጥሰት ከርቸሌ ልኮ አስኮብልሎ፣
ከምንም በላይ ደንብ መከበር አለበት ብሎ።

ዛሬ ገዳዮችን ከፊታ  ሕጉን እያፈረሰ፣
ምን መመሪያ ሆነ  ቃሉን በቃል ካበሰ?
ምን ሕግ ሆነ  ሲጠቅም የሚጠቀስ፣
ሲያስፈልግ የሚጣመም እንዳሻ  የሚቀበስ።

እኔስ አልማርኩም አይማረኝ የወንድም ደም አለብኝ፣
ይቅርታ  የለኝም ለፋሽስት ጨካኝ ብላችሁ ፍረዱብኝ፣
እኔስ አልምርም አይማረኝ የእህቶቹ  ደም ሳይመለስ፣
የእናት ያባት የግፍ ለቅሶ ኤሎሄው ሳይታበስ፣
የሙታን ፍትሃት ሳይደረግ ባጎበር ሳይለቀስ!!!!!!!!!!!!!!!!